# “የጨዋ ፖለቲካ - ለመንግሥት ስልጣን አይታገልምን?”

አምባገነን ገዥዎች የመንግሥት ስልጣን ይዘው የብዝበዛ መረባቸውን ዘርግተው፡ ለዚህም ስኬታማነት የአፈና ተቋማቸውን አጠናክረው ሕዝብን እንዳይናገርና እንዳይጽፍ ለጉመው፡ መብትና ነፃነቱን እስካፈኑት ድረስ በአንፃሩ መከራውና በደሉ እያንገፈገፈው ሕዝብ፡ ከጊዜ ወደ ጊዜ ሊሸከመው ከሚችለው በላይ ሲሆንበት፡ አገዛዙ በስዩመ እግዚሃብሔር ስም ይምጣ፡ በኢትዮጵያ ትቅደም ወይም በአዲሲቷ ኢትዮጵያ ሁሉም የችግሩና የብሶቱ አባባሾች እስከሆኑ ድረስ ሕዝብ ይታገላል። ያምፃል። በትንንሽ ተቃውሞ፡ በመለስተኛ ጥያቄዎች፡ በአካባቢ ችግሮች እያተኮረ የሚነሳ የሕዝብ ጥያቄ ምላሹ እስርና ግድያ እየሆነ በተጨማሪ በረሃብና በበሽታ እየተቀጣ፡ ሰጥ ለጥ ብሎ እንዲገዛ መከራ ሲወርድበት የጥያቄው አድማሱ ይሰፋና መብትና ነፃነቱን ለማስከበር አማራጩ የራሴ የሚለው መንግሥት መመስረት ላይ ይራመድና የፖለቲካ ሥልጣን ጥያቄ ይነሳል። ሕዝባዊ መንግሥት መፈክር ቀዳሚ ቦታውን ይይዛል። ይህ ደግሞ ከዛሬ 40 ዓመት በፊት የተነሳና ዛሬም መስዋዕትነት እየተከፈለበት ያለ ጉዳይ ለመሆኑ ለአፍታም መዘንጋት አግባብነት የለውም። ይህንን ያነሳ ሕዝብ ደግሞ የመንግሥት መቀያየር፡ የጉልቻ መለዋወጥ፡ መሠረታዊ ለውጥ ያመጣል፤ ወይም የሀገርና ሕዝብ ችግር ይፈታል ብሎ ስለማያምን አያረካውም። ሥር ነቀል ለውጥ ይፈልጋል። በተደጋጋሚ በስሙ እየነገዱ፡ መፈክሩን እየቀሙ፡ አለንልህ እያሉ ሊያሞኙት ከተነሱት ደርግና ኢሠፓ ለጥቆም አዲስቷ ኢትዮጵያ ብለው ሊከፋፍሉትና እርስ በርስ ሊያናክሱት ጫንቃው ላይ ከተፈናጠጡት ብዙ ተምሯል። ማነው እውነት ለሀገርና ለመብቱ የታገለለት፡ የሚታገልለት፡ ማነው በስሙ የሚነግድበት፡ የሚያሾፍበት ጠንቅቆ የሚያውቀውና ከትግል ተመክሮው ያገኘው የቀሰመው ልምድ መኖሩን መዘንጋት አንዳንድ ፖለቲከኞችን አዘቅት እየወረወረ ነው።

“ምጥ ለናቷ አስተማረች እንዲሉ”፡ ለአለፉት 40 ዓመታት ለመብትና ነፃነቱ እየታገለ ያለን ሕዝብና የሕዝብ ኃይል ስለመታገልና ስለትግል መራራነት ከራሱ ከባለቤቱ ተመክሮ ለመቅሰም ከመዘጋጀት ይልቅ የተገላቢጦሽ ለመስበክና ለማስተማር ድፍረቱን ካገኘንም ሀቁንና ነባራዊውን እውነታ የሳትን መሆኑን ማወቅ ያሻል።

በረሃብ እየተሰቃየ ላለ ሕዝብ፡ ደረቅ እንጀራ በበርበሬ እየናፈቀው ለመጣ ሕዝብ፡ የአገሪቷ ኢኮኖሚ በዓመት ይህን ያህል ዕድገት አሳይቷል፤ በመድሃኒትና በሕክምና እጦት በበሽታ እየረገፈ ላለ ሕዝብ በዓመት ይህን ያህል ሆስፒታሎች ገነባንልህ፤ ድህነትን መለያው ላደረገ ሕዝብ ትኩረት ተሰጥቷቸው ሊገነቡ የሚገባቸውን የልማት አውታሮች ላይ ከመረባረብ ይልቅ ሆቴሎችና ሕንጻዎች ዓይተህ ድህነትህን ቅረፍ ተብሎ ሲዘፈንለት፤ ከጉድጓድና ወራጅ ውኃ ያልተላቀቀን ሕዝብ፡ የንፁህ ውኃ አቅርቦታችን ይህን ያህል ጨምሯል፤ እየተባለ በደርግ ለ17 ዓመት የተዘፈነለት ዜማ በወያኔ 16 ዓመት ሲደገምለት፡ ሰው ለሀገሩ ባዳ ይሉ ዘንድ ይህ ሁሉ ዲስኩር የትኛዋ ኢትዮጵያ ላይ እየተካሄደ እንደሆነ ግራ እስኪገባው ድረስ ውሸትና የሀሰት ፕሮፓጋንዳ ሲንቆረቆርለት፡ ጨኸትና ወሬ ምግብ አልሆነውምና፡ የጥቂቶችም ወያኔን ዘለፋ መብትና ነፃነት ገላጭ አልሆነለትምና፡ እንደትላንቱ ዛሬም እየታገለ ነው። ላም አለኝ በሰማይና የተስፋ ዳቦ ዲስኩር ችግሩን ቀራፊዎች ሆነው አላገኛቸውምና ሕዝብ ሲታገልና ሲያምጽ ከማንና ለምን መሆኑን መረዳት የተሳነን የፖለቲካ አቀንቃኞች ባንሆን ይመረጣል። የፖለቲካውና የሀገር ዕይታችንም ጠባብ ከሆነም ድክመታችንን ይዘን ቢያንስ ለወያኔና ወይም ለዳግም አምባገነንነት ባናሸረግድ ይመረጣል።

የሕዝብ ትግል የሚወልዳቸው የፖለቲካ ድርጅቶች ከራሱ ከሕዝቡ ተፈጥረው ራሱን አታግለው ሲታገሉለት፡ በጽናት ለሕዝብና ለሀገራቸው ዓላማ ሲቆሙለት፡ በአምባገነኖችና በባዕዳን ድለላና

በግላዊ ጥቅም ትግሉን አሳልፈው ሳይሸጡበት እስከ መጨረሻው ደም ጠብታ ታግለው ሲያታግሉት ይመካባቸዋል፡ አለኝታዬ ይላቸዋል። ለዚህ ለሚከፈል መስዋዕትነት ደግሞ "የጀግና ዕረፍቱ ሞቱ" ብሎ ይቀበለዋል፡ ተቀብሎም ትግሉን ያፋፍመዋል እንጂ ጠላት "ባየለ" ቁጥር ስልቱ በመቻቻል ፖለቲካ ለወያኔ ማደር ሳይሆን፤ በስልታዊ አስተሳሰብ፡ በሰጥቶ መቀበል ፖለቲካ እጅን አጣጥፎ እንዲያጨበጭቡ፡ እግርን አኮራምቶ እንዲራመዱ መስበኩ "ከእጅ አይሻል ዶማ" ሌላም ካስፈለገ "አመድ በዱቄት ይስቃልን" ያስተርታል። በጨዋ ፖለቲካ ስም "የምናደርገው ትግል በምንም ዓይነት የሥልጣን ትግል አይደለም።" ተብሎ የፖለቲካ ድርጅት መሪዎች ነን ባዮች ሲያቅራሩብን ከሕዝብ ፍላጎት ይልቅ የራሳቸው የኑሮ መዛባት ያሳሰባቸው ለመሆኑ ሌላ አብራሪና ተርጓሚ አያስፈልገውም።

ትግል ዓላማ ያሻዋል፡ ትግል ራዕይ ያሻዋል። ዓላማውንና ግቡን ያወቀ፡ የሀገርንና የሕዝብን ጥቅም ለማስጠበቅ አለሁ ያለ የፖለቲካ ድርጅት ደግሞ፡ ዳግም በሕዝብ ስም ሊቀላምድ ሲዘጋጅ፡ በእኔ አውቅልሃለሁ ሹፈት ሊያታልል ዳር ዳር ሲል፡ አውቀው ሊያንቀላፉ ሲሞክሩ ቢቀሰቀሱ አይሰሙምና መፍትሔው እንዲህ አይነቱን አባጣ ጎርባጣ ማንሳትና፡ ከየቦታው የተሰባሰቡ የታሪክ ቆሻሾችን መጥረግ ብቻ ነው። ይህ ታዲያ ስልታዊ ማፈግፈግን ሳይሆን ስልታዊ ጥንካሬን ይጠይቃል። ይህ ታዲያ በስልታዊ መቻቻል ስም ለወያኔ እጅ መስጠትን ሳይሆን የትግል በትር፡ የጽናት በትር ማንሳትን ይጠይቃል። ይህ ታዲያ ለዳግም የወያኔ የምርጫ ትርዕይት መንደርደርን ሳይሆን በምርጫ የተገኘን ድል ማስከበርን ይጠይቃል። ይህ ታዲያ ወያኔ ፓርላማ ገብቶ ማጨብጨብን ሳይሆን ወያኔን አውድሞ ሕዝብን የፖለቲካ ሥልጣን ባለቤት ማድረግን ይጠይቃል። በጨዋ ፖለቲካ ስም ለወያኔ ተገዙ፡ ወያኔን አጅቡ፡ ወያኔን በጠላትነት አትፈርጁ፡ ሀገርን ለባዕዳን ስጡ፡ ዲስኩር "የደንቆሮ ለቅሶ መልሶ መላልሶ" ያሰኛልና ሹፈቱ በሕዝብ ላይ ሳይሆን በራስ መሆኑን ልንገነዘብ ግድ ይላል።

ወያኔ ለኢትዮጵያና ለሕዝቧ ካለው ጥላቻና ንቀት በተጨማሪ ለባዕዳን ሰጋጅና አምላኪ መሆኑን የተረዳነው ዛሬ አይደለም። ወያኔ ከኢትዮጵያዊው ዜጋ ይልቅ ባዕዱን የሚመርጥበት ምክንያት እያደረገ ላለው የጥፋት ሴራው ንፁህ ዜጋ አይካፈለኝም ብሎ ስለሚሰጋ ነው። ይህ የወያኔ ፀረ-ኢትዮጵያ ጠባይ ዛሬም ቢሆን ፈጽሞ አልተለወጠም። በመሆኑም ሀገር ወዳድ ኃይሎችና ወያኔ ሊስማሙ የሚችሉበት ሁኔታ ዛሬም የለም። ስለዚህ ዛሬም ቢሆን የሕዝባዊ ትግል ዋና ዓላማና ግብ የወያኔን አገዛዝ ማስወገድ መሆን አለበት። ለባዕድ ያደረና ሀገራችንን የሚጠላ ቡድን በገዥነት ሊቀጥልብን መፍቀድ መቻልና መሸከም ከቶም የለብንም። አጋጣሚንና ቀን እየጠበቁ ብቅ ለሚሉ ከሃዲዎችና ባንዳዎች ዛሬም ከ16 ዓመት የግፍ አገዛዝ በኋላ፡ በሕዝብ ደም መጨማለቁን በአደባባይ ላሳየ አገዛዝ እንዲሰገድለት ሲወተውቱን "ምንኛ ፖለቲካውን እንጨወትበታለን፡ ሞኝ ሁላ" ብለው መነሳሳታቸው ሌላው ቢቀር ከራሳቸው የቅርብ ጊዜ ከሃዲ መማር ያቃታቸው ናቸውና ራሳቸውን ወደ ማጥ ይዘው ይገባሉ፡ እንደ ሙቀጫ ይንከባለላሉ እንጂ የሕዝቡን ትግል እንደማያዘናጉ ልናሳስባቸው እንወዳለን። ለእኛ የሚታየው እንዲታያቸው፡ ለእኛ የሚሰማው እንዲሰማቸውና ከሕዝብና ከአንድነት ጐራው ጋር በቁርጠኝነት በመቆም ሳይፈሩ ሀገርና ሕዝብ እያወደመ ያለውን ወያኔ ለማውደም ስልፋቸውን ማስተካከል እንደሚገባ ማሳሰቡም፡ ማስገንዘቡም ግድ ይሆናል። ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ በአሁኑ ጊዜ ወያኔን በተመለከተ ምንም ብዥታ የለውምና።

የግንቦት 97ን ሂደት አይተን ይቅርና ከዚያም በፊት መለስ ዜናዊ በተዓምር ዲሞክራሲያዊ ሆኖ በሀገራችን ነፃ ምርጫ እንዲካሄድ ይስማማል የሚል ቅዠት ውስጥ ባንገባም ይህን ሕልም አድርገው ወያኔን ሊያቅፉ የሚራወጡ ድርጅቶችን ዳግም እያየን ነው። አሁንም በድርድርና በባዕድ ተፅዕኖ መለስ በምርጫ ስልጣኑን ይለቃል ብለው የሚያስቡ ድርጅቶች ያሉ ሲሆን

በመራራ ትግል ካልሆነ ወያኔ ከቤተ መንግሥት አይወጣም ባይ ግን ብዙሃኑ ሕዝብ ነው። ለዚህ ሂደታቸው ደግሞ ዘርፈ ብዙውን የሰላማዊ ትግል ጉዞ ከምርጫ ፖለቲካ ጋር እያምታቱ የሕዝባዊ አመጽን ትግላዊ ስልት እንደ ጠረኛ ሊፈርጁ ይከጅላሉ።

ብዥታ የድርጅቶች፡ ንቃት የሕዝብ በሆነበት ተጨባጭ ሁኔታ የትግሉ ሂደት ጎርባጣ መሆኑ አይቀሬ ነው። አዎ ለወያኔ እሹሩሩ፡ ለባዕዳን ልመና እራሳቸውን ያስገዙትን ጎርባጣዎች ማንሳትና ከየቦታው መጠራረግ አስፈላጊ ነው። አዎ ይህ ግን ብዙ ትግል ይጠይቃል። ስልታዊ መለሳለስን ሳይሆን መራራ ትግልን፡ መለስን ለመጨበጥ እጅ መዘርጋትን ሳይሆን በቡጢ ብሎ ለመጣል ቁርጠኝነት ማግኘትን፡ ተፍለቅልቆ መለስ ፊት ለመቆም ሳይሆን ክብርና ኩራትን ተላብሶ መለስን ለማንበርከክ መነሳሳትን ይጠይቃል። ወያኔን ከሀገራችንና ሕዝባችን ጫንቃ ለማስወገድ በትግል የተገኘን የሕዝብ ድል ለወያኔ አስረክቦ ውርደትንና ቅሌትን ለመቀበል የሚደረግ የሰጥቶ መቀበል ትግል ሳይሆን ሕዝባዊ አመጽን፡ ሕዝባዊ መነሳሳትን ለማጀብ ጥረትን ይጠይቃል።

የወያኔን አጋዚ የሚችለው የለም፡ የወያኔን ሀብትና መሣሪያ መቋቋም አንችልም፡ ወያኔ ባዕዳን አይዞህ ይሉታልና ያላቅማችን አንጠራራ፡ የማይወጡትን ዳገት ከመሞከር ይልቅ የሚሰጠንን ተቀብለን፡ የሚለንን አሜን ብለን፡ ተጐንብሶ ለመገዛት፡ ሰጥ ለጥ ብሎ ለመረገጥ የመቻቻል ስብከት ለሚያላዝኑ፡ ለግላዊ ፍላጎታቸው ለተቆጩ ሕዝብን አታዘናጉ እንላለን።

ድርጅቶች ተከርችሞ ያለው የወያኔ የለውጥ በር ገርበብ ብሎ ከታያቸው፡ መረር ላለው ትግል ሀሞቱም ወኔውም ካጠራቸው፡ መስዋዕትነት ጭምት ካደረጋቸው፡ ከግንቦት 97 ምርጫ ትርዕይትና የትግል ተመክሮ የተማሩት ፍርሃትን፡ ማፈግፈግን፡ መለሳለስን፡ ማጐብደድን፡ እጅ መስጠትን፡ ቅሌት መቀበልን ከሆነ፡ ከከርቸሌና ቃሊቲ እስራቸው ያካበቱት ተመክሮ ወያኔን ይቅርታ ጠይቆ ለመስገድ፡ ባዕዳንን እባካችሁ አስገቡን ብሎ ለመማፀን ከሆነ ሕዝብንና ሀገርን ሊመሩ ቀርቶ የሕዝብ ትግል ላይ የሚደነቀሩ ጋሬጣዎች ናቸውና በወቅቱ ትግል የሚፈለጉ አይደሉም።

የሕዝብ ድርጅት በትግል ሂደት ውስጥ እስሩንም፡ መከራውንም፡ መስዋዕትነቱንም ፡ እየከፈለ ሁሌም ከሕዝብ ተዋህዶ፡ ሕዝብን አነሳስቶ፡ የሕዝብ መከራ ኖሮ፡ ታግሎና ተሰቃይቶ ትግሉን የሚያፋፍምና አስፈላጊውን መስዋዕትነት የሚከፍል ነው። የሕዝብን ትግል መምራት ማለት በየአዳራሹ ከረባት አስሮ ማደናገርና ከገዥዎች ጋር መከራከር፡ ወያኔን መክረን ልቦና እናስይዘዋለን ብሎ መደስኮር፡ የጨዋ ፖለቲካ እያሉ ሕዝባዊ ትግልን ለማሽመድመድ መነሳሳት፡ የሰለጠነ ፖለቲካ እያሉ የሰለቸን የባዕድ ኤምባሲ ኮክቴል ግብዛ ላይ ለመደስኮር መዘጋጀት፡ አረመኔውን አገዛዝ በየጋዜጣውና በየቴሌቪዥኑ እየተቹና እየተረቡ የሰለቸን የማዘናጋት ጨዋታ ለመጫወት መነሳሳት አይደለም።

በወያኔ ሰራሽ ረሃብና በሽታ እየተሰቃየና እየረገፈ ያለን ሕዝብ ወያኔን ለመጣል ካመጽህ ትታሰራለህ፡ ትሞታለህ ብሎ መስበክ የሞት አማራጭ መስጠት ነው ወይስ ለወያኔ ዕድሜ መራዘም አስተዋጽዎ ማድረግ? ዛሬ አምርሮ መታገል በሚገባንና ሀገራችንን ታይቶ ከማይታወቅ ጥፋት ለማዳን መነሳሳት ሲጠበቅብን ከአሽባሪው ገዥ ቡድን በባሰ ሕዝብ ሰላም ናፍቆታልና ያመረረ ትግልን አታንሱብን፡ በመቻቻል እንጓዝ ባይ ተቃዋሚ ድርጅቶች እውን ከሕዝብ ነው ወይስ ከወያኔ ሰልፋቸው?

በምርጫ ዲሞክራሲ ያገኙትን ድል በተቀጣጠለው ሕዝባዊ አመጽ መርቶ ለድል ለማብቃት ችሎታው ተሰኖት፡ የ299 መቀመጫዎችን ጥያቄ ወደጎን አርጎ ቢለማመጥም፡ በባለሰምንት ነጥብ መለመኛ እጅ ቢሰጥም ተንቆ ለሬዲዮና ለቴሌቪዥን ክፍሉ እስር ቤት የተወረወሩ ኃይሎች ዛሬም

የምርጫን ዲሞክራሲ ሊሰብኩን ሲቃጡ ብንስቅባቸው ትዝብት ላይ አንወድቅም። እኚህ ድርጅቶች ዋናው ማወቅ ያለባቸው ሀቅ ግን ሕዝብ ለመብቱ መታገል አለመሰልቸቱን ነው። ዛሬም የአቻምናው ግንቦት 97 ምርጫ ለምን ከሸፈ? ለሚለው መልስ ለመስጠት ያልፈለጉት ተቃዋሚዎች፣ ወያኔ በምንም መንገድ በምርጫ ፖለቲካ ሥልጣን እንደማይለቅ ለማመን አለመፈለጋቸው ከሕዝብ ፍላጎትና ትግል ለመራቅ ያላቸውን ዝንባሌ ጠቋሚ ነው። በግንቦት 97 ምርጫ ሕዝብ አሸነፈ። ከማሸነፍ በላይ ምንድን ነው የተፈለገው? ይህ የሕዝብ ድምጽ በመስረቁ ዳር እስከዳር ሕዝቡ ለአመጽ ተነሳሳ፣ ትግሉን አጧጧፈ። በወቅቱ ይህን የሕዝብ አመጽ ለመምራትና ከግብ ለማድረስ ከመነሳሳት ይልቅ ትግሉ ላይ ቀዝቃዛ ውኃ የቸለሱት የትግሉ አርበኞች ነን ባዮች ዛሬ ደግሞ ስለ መጪው የወያኔ ምርጫ ሲተርኩ አለማፈራቸው ለሕዝብና ለሀገር ያላቸውን ንቀት አመልካች ነው።

በግንቦት 97 ምርጫ ሕዝቡ ሙሉ ድምጹን ስለሰጣቸው የተበሳጨት ከወያኔ ይልቅ እኚህ ተቃዋሚዎች ይመስላሉ። በመጠኑ፣ በዕቅዳቸው ይዘውት እንደነበረው ሰጥቷቸው ቢሆን ኖሮ ፓርላማቸው ገብተው የቴሌቪዥን ትግላቸውን እያካሄዱ ለቀጣዩ ምርጫ ደግሞ ሌላ ውድድር ነበር የፈለጉት። ግና ሕዝቡ አሳፈራቸው። በሙሉ ድምጽ መረጣቸው። ይህ ድል እንዲከበር ደግሞ ሕዝቡ ያኔም አሁንም ፍላጎቱ ነውና ሳያስቡት፣ ሳይዘጋጁ በገቡበት አጣብቂኝ የለመዱት ግላዊ ሕይወታቸው መዛባቱን፣ መቃወሱን መቀበል ይገባቸው ነበር። ተቀብለንማ መስዋዕት ከፍለናል፣ ታስረናል ከተባለ ደግሞ "ጥፋተኛ ነን፣ ይቅር በሉን፣ ሁለተኛ አይለመደንም" ብሎ መፈረም ምን ያህል የግል ኑሯቸው መዛባቱ ያሳሰባቸው እንጂ የሕዝብ ድል የታያቸው አለመሆኑ የሰሞኑ ሂደታቸው ጠቋሚ ምስክር ነው። እነሱም እንደተመኙት ወያኔም ዕድሜ ሰጥቶት ለ2010 ምርጫ በፈለጉት አካሄድ ካደረሳቸው ደግሞ የራሳቸውን ኮሮጆ በወያኔ የሚቀይሩት እንደነኚህ ዓይነቶቹ የተቃዋሚ ድርጅቶች እንደሚሆኑ መገመት አያዳግትም። ከግንቦት 97 ምርጫ የተማሩት ቢኖር ወያኔ መሸነፍ እንደሌለበት ነዋ!

የመለስ አገዛዝ በሕዝብ ድምፅ ከሥልጣን ተወግዷል። ይህን ተግባራዊ ማድረግ ነው የተቃዋሚ ኃይሎች ግዴታና ሥራ። ለዚህም መንገዱ ዕብሪት ያደነቆረውን አገዛዝ ልምምጥ ሳይሆን፣ ሕዝብን አቅፎ ታሪካዊና እርድ አንቀጥቅጥ ሕዝባዊ አመፅን ማካሄድ ነው። ሌላ አማራጭ የለም፣ ባርነትን፣ ሀገር ማጣትን አማራጭ ነው ብለን መውሰድ በጅግኖች ደም የተፃፈውን ታሪካችንን ልናበላሸና ልናረክስ ካልሆነ በስተቀር። ይህን ደግሞ የኢትዮጵያ ሕዝብ መቸም አይቀበለውም። የኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል ድልን ሳይቀዳጅ ትጥቃችንን እንፈታለን፣ ትግላችንን እናለዝባለን ማለት ዘበት ነው። ኃይል የሕዝብ ነው። ሰልፋችን ከሕዝብ ጋር ከሆነ ኃያል እንሆናለን። በማመፅ ፈንታ ሰበቦች ደርድረን የመጎንበስን፣ የእጅ መስጠትን ቅሌት ከተቀበልን ደግሞ ታሪክና ሕዝብ ከመታዘብ ሌላ አንቅረው ይተፉናል ማለት ነው። ይህን ሀቅ ድርጅቶች መቀበል አለባቸው። ዛሬ ሊሞት ሲል የመለስ አገዛዝ ጠባዩን ሊለውጥ አይችልም። አደብ አይገዛም። ተው ሲሉት አይተውም። በተቃኘበት ፀረ - ሕዝብ፣ ፀረ - ኢትዮጵያ ጎዳና ይነጉዳል እንጂ ገደሉም ጥፋቱም ታይቶት አይታረምም።

ትግላችን ሕዝብን መሰረት ላደረገ የፖለቲካ ስልጣን መሆን ይገባዋል!
ወያኔ የሀገርና የሕዝብ ጠላት ነው!
ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!!